አጭር - ቅጽ (04/04/2023)　　　　Amharic

*(ይህ ቅጽ ከ ሳይንሳዊ ሙከራ ባለጉዳይ የመብቶች ሕግ እና IRB የጸደቀ የስምምነት ሰነድ ጋር መያያዝ ይኖርበታል)*

# በምርምር ጥናት ለመሳተፍ ስምምነት

የባለጉዳዩ ስም:- ________________________________ IRB ጥናት #:- ________________

የህክምና መዝገብ/ባለጉዳይ ID #:- ____________________________

እርስዎ ወይም ልጅዎ በምርምር ጥናት ውስጥ እንዲሳተፉ እየተጠየቁ ነው። አንድ የምርምር ጥናት ሳይንቲስቶች (ሃኪሞች፣ ነርሶች እና ሌሎች ባለሙያዎች) ነገሮች እንዴት እንደሚሰሩ ለመገንዘብ እና አዲስ እውቀትን ለመገብየት የሚሞክሩበት ነው። አንድ የምርምር ጥናት ሰውነት እንዴት እንደሚሰራ፣ የበሽታ መንስኤ ምን እንደሆነ፣ በሽታ እንዴት እንደሚታከም፣ ወይም ስለተወሰኑ ነገሮች ሰዎች ምን እንደሚያስቡ እና እንደሚሰማቸው የሚመለከት ሊሆን ይችላል።

እርስዎ ወይም ልጅዎ በዚህ ምርምር ጥናት ውስጥ ይሳተፉ እንደሆን ከመወሰንዎ በፊት፣ ምርምር አድራጊው ሊነግርዎ የሚገባ (i) በምርምር ውስጥ ለምን እንደሚሳተፉ ወይም እንደማይሳተፉ ለመገንዘብ የሚረዱዎት ቁልፍ መረጃዎች (ii) የምርምር ጥናቱ ዓላማዎች፣ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች - እነዚህ የአሰራር ሂደቶች ተብለው ይጠራሉ፣ እና ምርምሩ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚዘልቅ፤ (iii) በሳይንሳዊ ሙከራ ላይ ያሉ ማናቸውም የአሰራር ሂደቶች (በሙከራ ያሉ)፣ ማንኛውም ሊደርስ የሚችል ስጋት፣ ምቾት ማጣቶች፣ እና የምርምሩ ጥቅሞች፤ (iv) ማናቸውም ሌላ አቅም ያላቸው ጠቃሚ የሆኑ የአሰራር ሂደቶች ወይም ህክምና፤ እና (vi) የእርስዎ ግላዊነት እንዴት እንደሚጠበቅ፤ (vii) ሊታወቅ የሚችል የግል መረጃ ወይም ናሙናዎች ለወደፊት ምርምር ሊቀመጡ ይችሉ እንደሆን ወይም ለዛ ሌላ ምርምር ያለስምምነት ከምርምር አድራጊዎች ጋር ይጋሩ እንደሆን።

ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ምርምር አድራጊው ስለ እነዚህ ጉዳዮችም ሊነግርዎ ይገባል (i) ጉዳት ወይም እንከን ከደረሰ ማንኛውም የሚገኝ ክፍያ ወይም ህክምና፤ (ii) ያልታወቁ ስጋቶች የመኖራቸው እድል (iii) ምርምር አድራጊው የእርስዎን ተሳትፎ ሊያስቆምበት የሚችልባቸው ሁኔታዎች፤ (iv)እርስዎ ላይ የሚኖሩ ማናቸውም ተጨማሪ ወጪዎች፤ (v) መሳተፍዎን ለማቆም ቢወስኑ ምን እንደሚፈጠር፤ (vi) የእርስዎ የመሳተፍ ፈቃደኝነት ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ስለሚችሉ አዳዲስ ግኝቶች መቼ እንደሚነገርዎ፣ እና (viii) የእርስዎ የተፈጥሮ ናሙናዎች ለንግድ ትርፍ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉበትን እውነታ እና በዛ የንግድ ጥቅም ውስጥ እርስዎ ይጋሩ እንደሆን፤ (ix) ምርምሩ የዘረመል ሙሉ ቅደም ተከተል እርካቦችን የሚያካትት ስለመሆኑ።

ለመሳተፍ ከተስማሙ፣ ለእዚህ ጥናት በእንግሊዝኛ የተጻፈ የጸደቀ ስምምነት እና የዚህ ሰነድ የተፈረመበት ቅጂ ሊሰጥዎ ይገባል።

ስለ ምርምሩ ወይም ከተጎዱ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ጥያቄዎች ካሉዎት ________________________ በ ________________________ በማንኛውም ጊዜ ሊያነጋግሩ ይችላሉ። ምርምር እንደሚካሄድበት ባለጉዳይ ስለ መብቶችዎ ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት የተቋሙን ግምገማ ቦርድ በ (323) 442-0114፣ በኢሜይል በ hrpp@usc.edu ማነጋገር፣ ወይም በሚከተለው አድራሻ በደብዳቤ መላክ ይችላሉ:-

USC Institutional Review Board (IRB)
3720 South Flower Street
CUB325 / MC0702
Los Angeles, CA 90089-0702

በዚህ ምርምር ውስጥ የእርስዎ ተሳታፊነት በፈቃደኝነት ነው (በእርስዎ በግል ምርጫ)፣ እና ለመሳተፍ ፈቃደኛ ባይሆኑ ወይም ለማቆም ቢወስኑ የሚያጡት ጥቅማጥቅሞች ወይም ቅጣት የለብዎትም።

ይህን ሰነድ መፈረም ማለት የምርምር ጥናቱ፣ የላይኛውን መረጃ ጨምሮ፣ በቃል ለእርስዎ ተገልጾልዎታል፣ እና በፈቃደኝነት ለመሳተፍ ተስማምተዋል ማለት ነው።

________________________________________　　　　________________________

የተሳታፊው ፊርማ　　　　ቀን

________________________________________　　　　________________________

በሕግ የተፈቀደለት ተወካይ ፊርማ　　　　ቀን

__________________________/_____________________　　　　________________________

ስም በእጅ ጽሁፍ/የምስክር ፊርማ　　　　ቀን

አጭር - ቅጽ (04/04/2023) Amharic

*(ይህ ቅጽ ከ ሳይንሳዊ ሙከራ ባለጉዳይ የመብቶች ሕግ እና
IRB የጸደቀ የስምምነት ሰነድ ጋር ማያያዝ ይኖርበታል)*

የስምምነት ቅጽ ቅጂዎች ግልባጭ፡- 1) ለቤተሰብ የሚሰጥ፤ 2) የህክምና መዝገብ፤ 3) የምርምር አድራጊው ዶሴ።